# የራይድ ኦን (Ride On) የተጠቃሚ መመሪያ




## ከእኛ ጋር ይገናኙ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትራንስፖርት ዲፓርትመንት

ወደ MC311 በ
240-777-0311 • 311 ይደውሉ

101 Monroe St • 5th Floor
Rockville, Maryland 20850

RideOnBus.com

@RideOnMCT

## ሰብስክራይብ ያድርጉ

የኢሜይል ማሳወቂያዎችን ለማግኘት፦
MontgomeryCountyMD.gov/govdelivery

የአጭር ጽሁፍ መልእክት ማሳወቂያዎችን ለማግኘት፦
MONTGOMERY RIDEON ብለው አጭር ጽሁፍ መልእክት ወደ 62463 ይላኩ

*የመልእክት እና የዳታ ተመን ክፍያዎች ሊተገበሩ ይችላሉ። መልእክቶች በተለያዩ ጊዜያት ሊላኩ ይችላሉ። ለእገዛ HELP ብለው መልስ ይስጡ ወይም በ support@granicus.com ያግኙን፣ መልእክቶችን መላካቸው እንዲቋረጥ "STOP" በማለት መልስ ይስጡ። ለበለጠ መረጃ Montgomery Wireless Terms and Conditions and Privacy ፖሊሲን ይጎብኙ።*

MCDOT

Ride On Montgomery County Transit

## ክፍያዎች

| መግለጫ | ክፍያ |
|---|---|
| ሁሉም የኤምሲዲኦቲ(MCDOT ) አውቶቡሶች ራይድ ኦን ፣ ራይድ ኦን ኤክስትራ፣ ፍሌክስ፣ እና ፍላሽን ጨምሮ። | ነፃ |

**ሁሉም የራይድ ኦን አውቶቡሶች ነፃ ቢሆኑም፣ ከፌብሩወሪ 1፣ 2026 ጀምሮ፣ ሁሉም ሰው የስማርትሪፕ፣ የወጣቶች ክሩዘር ስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርድ፣ የአረጋዉያን(ሲኒየር) ስማርትሪፕ፣ የተቀናሽ (Reduced) ስማርትሪፕ ወይም የሜትሮ አክሰስ ስማርትሪፕ ካርድ ሁሉም ሰው የግዴታ መያዝ አለበት እና በካውንቲ ውስጥ በሚገኙ ሜትሮባሶች ላይ ነፃ ለመጓዝ የክፍያ ሳጥኑን ማስነካት አለባቸው።ተሳፋሪዎች ከስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርዶቻቸው ላይ ምንም አይነት ክፍያ አይወሰድም።ካውንቲው ለጉዞዎች ዉማታን(WMATA ) ይከፍላል፣ ስለዚህ ትክክለኛ ቆጠራ ለማድረግ በክፍያ ሳጥኑ ላይ ማስነካት ያስፈልጋል።እነዚህን ካርዶች በማሳየት ብቻ ማሳፈር አቁመናል፤ ሊያሳዩ ከሞከሩ እንዳይገቡ ይከለከላሉ።የሜትሮባስ (Metrobus) ኦፕሬተሮች የታሪፍ ክፍያን ያስፈጽማሉ።**




በሴፕቴምበር 2025 ተሻሽሏል፡፡

ራይድ ኦን (**Ride On**) ቅዳሜና እሁድን እና የበዓላት ቀናትን ጨምሮ በካውንቲው ውስጥ ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምንም ክፍያ የሌለው የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጥ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ዋና የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ነው።የትራንዚት አገልግሎት የስራ ክፍል ከ 385 በላይ በካውንቲው ባለቤትነት የተያዙ እና የሚተዳደሩ አውቶቡሶችን ያቀፈ እና በዓመት ከ 18 ሚሊዮን በላይ ጉዞዎችን የሚያደርገውን የካውንቲውን የራይድ ኦን (Ride On) አውቶቡስ ስርዓት ያቅዳል፣ መርሐግብር ያወጣል እና ያስተዳድራል።የራይድ ኦን (Ride On) አሰራር በካውንቲው ውስጥ ባሉ ሌሎች የህዝብ ማመላለሻ አቅራቢዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሟላት የታቀደ ነው።ከ 80 በላይ የጉዞ መንገዶች፣ ራይድ ኦን (Ride On) እንደ ሜትሮ መናኸሪያዎች የገበያ ማዕከሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የንግድ ቦታዎች፣ የጤና አጠባበቅ እና ሌሎችም ያሉ ቁልፍ መዳረሻዎችን ያገለግላል።ራይድ ኦን (Ride On) ለአጠቃቀም ቀላል የሆነ፣ የማንኛውንም ጊዜ የአውቶቡስ መከታተያ አፕልኬሽን፣ የራይድ ኦን ትሪፕ ፕላነር (Ride On Trip Planner) (በሞባይል እና በዴስክቶፕ ላይ መጠቀም የሚችሉበት) እና ድረ-ገጽ ላይ የራይድ ኦን ሪል ታይም (Ride On Real Time) አገልግሎትን ይሰጣል።የራይድ ኦን ትሪፕ ፕላነር (Ride On Trip Planner) የሞባይል አገልግሎት በጎግል ፕሌይ እና በአፕል አፕልኬሽን ማውረጃ ውስጥ ይገኛል።

ራይድ ኦን ኤክስትራ (**Ride On ext*Ra***) በሚያገለግላቸው መንገዶች ላይ ፈጣን ጉዞን የሚሰጥ ታዋቂ የሆነ ውሱን ማቆሚያ ያለው አገልግሎታችን ነው።ይህ አገልግሎት ከራይድ ኦን (Ride On) በተለየ ሁኔታ ውስን የሆኑ ቦታዎች ላይ ብቻ የሚቆም ሲሆን፣ ተሽከርካሪዎች የሚበዙበት ሰአቶች ወቅት(peak hours) የጉዞ ጊዜን ይቀንሳል።የራይድ ኦን ኤክስትራ (Ride On ext*R*a) አውቶብሶች ነጻ የዋይፋይ (WiFi) እና ቻርጅ ማድረጊያዎች ለተጨማሪ ምቾት ያቀርባሉ።ራይድ ኦን ኤክስትራ ራውት (Ride On ext*R*a Route) 101 የተባለው ከ MD 355 ከሌክ ፎረሰት (Lakeforest) ትራንዚት ሴንተር ወደ ሜዲካል ሴንተር ሜትሮ ጣቢያ 13 መቆሚያ ብቻ ያሉት ሲሆን ይህ መስመር በመሰረቱ ከ 80 መቆሚያ ፌርማታዎች አሉት። የጉዞ መንገድ 101 ተሽከርካሪ የሚበዛበት ጊዜ ከሰኞ እስከ አርብ በ 20 ደቂቃ ውስጥ ይመላለሳል። በተጨማሪም፣ የላይም (Lime) እና ፒንክ ኤክስትራ (Pink ext*R*a) መንገዶች፣ የተጀመሩት 2024 ላይ ሲሆን የግሬት ሰኒካ ትራንዚት ኔትወርክ (Great Seneca Transit Network) አካል ሆኖ በሼዲ ግሮቭ ሜትሮ (Shady Grove Metro) መንሃሪያ፣ በግሬት ሲኒካ ላይፍ ሳይንስ ማእከል (Great Seneca Life Sciences Center) እና በሼዲ ግሮቭ ዩኒቨርሲቲ በኩል የሚያልፍ ነው።የላይም (Lime) እና ፒንክ (Pink) መንገዶች በራይድ ኦን (Ride On) 43፣ 63፣ እና 66 መንገዶች ላይ አብሮ የሚያልፍ ሲሆን ተሽከርካሪ የሚበዛበት ሰአት ላይ ከሰኞ እስከ አርብ ደግሞ በየ 15 ደቂቃ ሲመጣ፣ ቅዳሜ እና እሁድ በየ 30 ደቂቃ ይመጣል።ወደፊት በካውንቲው ዋና ዋና ኮሪደሮች ላይ ተጨማሪ የኤክስትራ (ext*R*a) የጉዞ መንገዶችን ይጠብቁ።

ራይድ ኦን ፍሌክስ (**Ride On Flex**) የመጀመሪያው ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የህዝብ ትራንዚት አገልግሎት ሲሆን በተመረጡ በግሌንሞንት/ ዊተን (Glenmont/Wheaton) እና በራክቪል (Rockville) ውስጥ ባሉ ዞኖች ውስጥ አገልግሎት ይሰጣል።ይህ አገልግሎት አገልግሎቱን የሚጠቀሙ ሰዎች ራይድ ኦን ፍሌክስ (Ride On Flex) መተግበሪያን በመጠቀም የመጓጓዣ አገልግሎት መጠየቅ ይችላሉ እናም ተጓዦችን ከትራንዚት ማእከሎች፣ የንግድ ማእከሎች፣ የመንግስት አገልግሎት እና ቤቶቻቸው ጋር በሚያገናኙ የፍሌክስ (Flex) ዞኖች ውስጥ ያደርሷቸዋል።ራይድ ኦን ፍሌክስ (Ride On Flex) ውስን የሆኑ የማቆሚያ ስፍራዎች ወይም ቋሚ የሆነ መርሀግብር የሌለው ሲሆን፣ በተለመዱ የአገልግሎት ሰአቶች በእለቱ ትራንስፖርት ሲጠሩ የሚመጣ ሲሆን፣ በራይድ ኦን ዜሮ (Ride On's zero) ፖሊሲ መሰረት በተለመዱ የአውቶብስ መስመሮች ላይ ተለዋዋጭ የሆነ የአማራጭ አገልግሎት ይሰጣል።የፍሌክስ (Flex) አውቶብሶች ዊልቸሮችን ማስተናገድ ይችላሉ እንዲሁም ነጻ ዋይፋይ (WiFi) አላቸው።በግሌሞንት/ዊተን (Glenmont/Wheaton) እና ሮክቪል (Rockville) ዞኖች ውስጥ ትራንስፖርት ለማግኘት የራይድ ኦን ፍሌክስ (Ride On Flex) አፕልኬሽንን አውርደው ይጠቀሙ ወይም ከሰኞ እስከ አርብ ከ 6 ኤኤም እስከ 7 ፒኤም ባለው ጊዜ፣ በ 240-301-3842 በመደወል መጓጓዣ ይጥሩ።እንደ ራይድ ኦን (Ride On) ማሻሻያ ጥናት መሰረት ተጨማሪ ፍሌክስ ዞኖች (Flex zones) ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዷል።

ራይድ ኦን ፍላሽ (**Ride On Flash**) የካውንቲው ፈጣን የአውቶብስ ትራንዚት (Bus Rapid Transit, RBT) አገልግሎት ሲሆን ፈጥነት እና ድግግሞሽ ያለው አገልግሎት በአገልግሎት መንገድ 29 ኮሪደር ላይ በሲልቨር ስፕሪንግ እና በርተስቪል መካከል ለመስጠት የተሰራ ነው።ፍላሽ (Flash) አውቶብሶች ልዩ የሆነ ወደ አውቶብስ አገባብን ከብዙ መግቢያ ጋር የሚያካትት ሲሆን በቀላሉ ለመግባት ያመቹ ዘንድ ደግሞ ዝቅ ያለ መሳፈርያ ያለው ፣ እንዲሁም ራይድ ኦን (Ride On) ፖሊሲ መሰረት ያለምንም ክፍያ የሚያካሂድ ነው።ለአውቶብስ ብቻ በሆኑ መንገዶች፣ በመንገድ መብራቶች ላይ የሚሰራ አውቶማቲክ ቴክኖሎጂ(transit signal priority) ፣ ዋይ ፋይ (WiFi) እና የብስክሌት መስቀያ ያለው የራይድ ኦን ፍላሽ (Ride On Flash) ለፍጥነት እና ውጤታማነት የተዘጋጀ ነው።ተጨማሪ የፍላሽ (FLASH) አገልግሎት ለሌሎች ዋና ኮሪደሮች አገልግሎት መስጠት እንዲችል ወደፊት ታቅዷል።

## ዛሬን ከእኛ ጋር ይጓዙ!

## RideOnBus.com



# እንኳን በደህና መጡ



የትራንዚት አገልግሎት ዲፓርትመንት አስፈላጊ የሆነ ተልእኮን በመያዝ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚያቀርብ ሲሆን ይህም ሰዎችን፣ ማህበረሰቦችን፣ የስራ ስፍራዎች፣ የትምህርት ተቋማትን፣ የመዝናኛ ስፍራዎችን እና ሌሎች ወሳኝ መዳረሻዎችን በማገናኘት ነው።ትራንዚት በተለይም ተሽከርካሪ በሚበዛባቸው ሰአቶች መንገድ ላይ ያሉ መኪናዎችን በመቀነስ የሞንትጎመሪ ካውንቲን መሰረተ ልማት ውጤታማነትን ከፍ ያደርጋል።በተጨማሪም ትራንዚት በአካባቢው ኢኮኖሚ ላይ እና የመኖሪያ አካባቢዎችን ምቹ በማድረግ ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

# የአውቶብስ አጠቃቀም

**ለእርስዎ ምቾት እና ደህንነት፦**

- ሌሎች በፍጥነት መሳፈር እንዲችሉ ወደ አውቶብሱ ኋለኛ ክፍል ይለፉ።
- አረጋውያን እና አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች ቅድሚያ ባላቸው መቀመጫዎች ላይ እንዲቀመጡ ያድርጉ።
- ሌሎች ሰዎች ቆመው እያዩ እባክዎን ከአንድ በላይ መቀመጫ አይጠቀሙ።
- የህጻናት መግፊያዎችን ከመተላለፊያዎች እና በሮች አካባቢ ያርቁ።
- ማጨስ፣ መመገብ፣ መጠጣት እና መትፋት አይቻልም።
- የድምጽ መሳሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የጆሮ ማዳመጫ ወይም ዝቅ ያለ የድምጽ መጠን ይጠቀሙ።
- በሚቆሙበት ጊዜ በአውቶቡሱ ውስጥ ካለው የደህንነት መስመር(safety line) ጀርባ ይሁኑ (የፌዴራል ህግ ነው)።
- አውቶቡሱ በሚጓዝበት ጊዜ ከአሽከርካሪው ጋር ንግግር ባለማድረግ አሽከርካሪው አውቶቡሱን በአግባቡ እንዲነዳ ይፍቀዱለት።
- ከአውቶብስ በሚወርዱበት ጊዜ፣ በጀርባው በር ይውረዱ እንዲሁም ከእርስዎ ቀጥሎ ለሚወርደው ሰው በሩን ይያዙለት።

# ተደራሽነት



ሁሉም አውቶቡሶች ተደራሽ ናቸው።በአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ህግ (Americans with Disabilities Act, ADA) እና የፌደራል ትራንዚት አስተዳደር መመሪያዎች መሰረት፣ ራይድ ኦን (Ride On) አንድ አካል ጉዳተኛ የሆነ ግለሰብ የሚሰጠውን አገልግሎት ማግኘት እንዲችል እና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በሚችለው መጠን ሁሉንም ማድረግ የሚችለውን ጥረት ያደርጋል።

# የጉዞ እቅድ ማድረጊያ መረጃዎች

እነዚህ መረጃዎች ጉዞዎትን ከቤትዎ፣ ከስራ ቦታ ወይም መንገድ ላይ ሆነው ለማቀድ እንዲችሉ ያስችሎዎታል።እነዚህ የአሰራር መሳሪያዎች በቋሚነት መሻሻያ እየተደረገባቸው መሆኑን እባክዎ ያስተውሉ።

- ራይድ ኦን ትሪፕ ፕላነር (Ride On Trip Planner)፣ tinyurl.com/rotripplanner
- ራይድ ኦን ሪል ታይም (Ride On Real Time)፣ RideOnRealTime.com
- ጎግል ካርታዎች (Google Maps)፣ www.google.com/maps/
- የሜትሮ ትሪፕ ፕላነር (Metro's Trip Planner)፣ www.wmata.com
- ለጉዞ እቅድ ድጋፍ MC311 የመረጃ ማእከልን ማግኘት ይችላሉ ይህም ሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ 311 ብለው በመደወል ወይም ከካውንቲው ውጪ ከሆኑ በ 240-777-0311 መደወል ይችላሉ።

በረዶ፣ አውሎ ነፋስ ወይም ሌሎች ራይድ ኦን (Ride On) የተለመደ ሳምንታዊ መርሀግብሩን እንዳይከተል የሚያደርጉ ልዩ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ፣ የአውቶብስ አገልግሎት በ'S' የአገልግሎት እቅድ ሊሰራ ይችላል (ይህም በእንግሊዘኛ እና ስፓኒሽኛ ይገኛል )።

# የሲስተም ካርታ

እባክዎትን www.RideOnBus.com – "Trip Planning" ገጽን በመጎብኘት የራይድ ኦን (Ride On)ን ኤሌክትሮኒክ ካርታ ማየት ይችላሉ።የራይድ ኦን (Ride On) መንገዶችን/መርሀግብሮችን ለማግኘት እባክዎትን "Ride On Schedules" ገጽን የሚከተለው ድረ-ገጽ ላይ ይመልከቱ። www.RideOnBus.com

# ስማርትሪፕ (SmarTrip®)

**ከጁን 29, 2025 ጀምሮ ራይድ ኦን (Ride On) የዋጋ ነፃ ፖሊሲ ተግባራዊ ሲሆን የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርዶች በራይድ ኦን አውቶቡሶች ላይ አይሰሩም።**

ስማርትሪፕ (SmarTrip®)– በዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ ላለው የሜትሮ እና ክልላዊ ትራንዚት አገልግሎት ለመጠቀም የሚያስችል መክፈያ መንገድ ነው።ስማርትሪፕ (SmarTrip®) በአካባቢው ውስጥ በትራንዚን መሄድን ቀላል ያደርጋል እና ገንዘብዎትን ይቆጥብልዎታል።በስማርትሪፕ (SmarTrip®) ተጠቃሚ ተጓዦች ይህን ተጠቅመው ለሜትሮሬል (Metrorail)፣ ለሜትሮ ባስ (Metrobus) እና ሜትሮ ጣቢያዎች ላይ ለመኪና ማቆሚያ መክፈል ይችላሉ።

- **የፕላስቲክ ካርዶች፣** የስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርድዎን በሜትሮ መግቢያ፣ የአውቶብስ ክፍያ መክፈያ ማሽኖች፣ የሜትሮ መኪና ማቆሚያ ላይ ባሉ ክብ የሆኑ ምልክቶች ላይ በማስነካት ይጠቀሙ።ለተጨማሪ መረጃ ይህን ድረ-ገጽ ይመልከቱ። https://www.wmata.com/fares/smartrip/faq.cfm
- **ሞባይል መክፈያ(Mobile Pay)፣** የሞባይል ስልክዎትን በሜትሮ የክፍያ በር ላይ፣ የአውቶብስ ክፍያ ማሽን ወይም የሜትሮ መኪና ማቆሚያ ጋራዦች ላይ በማስነካት ይክፈሉ።ለበለጠ መረጃ ይህን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፣ www.wmata.com/fares/mobilepay/
- **የሜትሮ ተጠቃሚዎች ወደ አውቶብስ በሚገቡበት ጊዜ የስማርትሪፕ (SmarTrip®)ካርዳቸውን በመክፈያ ሳጥን ላይ ማስነካት አለባቸው።** በአውቶቡስ ላይ የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ ማሳየት እና መግባት አይፈቀድም እና የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ ትክክለኛ አጠቃቀም ከፌብሩወሪ 2026 ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል።

## ስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ (የቀጠለ)

**ማስታወስ የሚገቡ ነጥቦች፡-**

- ስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ በተደጋጋሚ የሚሞላ ሲሆን እስከ $300 ድረስ ሊይዝ ይችላል።
- የተመረጡ የአውቶብስ እና የሜትሮ ማለፊያዎችን የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ በኦላይን መሙላት ይችላሉ።ካርዱ በአንድ ጊዜ እስከ ሁለት ማለፊያዎችን መያዝ ይችላል።
- ለደንበኞች አገልግሎት 1-888-SMARTRIP (762-7874) ብለው ይደውሉ ወይም በ smartrip@wmata.com ኢሜይል ያድርጉ።ለደንበኞች ድጋፍ አገልግሎት ካርዶች መመዝገብ አለባቸው።
- ደንበኞች አውቶብስ ውስጥ ወይም ሜትሮ ጣቢያዎች ያላቸውን ቀሪ ሂሳብ ማረጋገጥ እና ካርዳቸው ላይ ገንዘብ መሙላት ይችላሉ።
- ስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርዶ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ያለዎትን ቀሪ ሂሳብ መልሰው ማግኘት ይችላሉ።ያስታውሱ፡- ይህንን እድል ለመጠቀም ካርዱ ቀድሞ መመዝገብ አለበት።

**ካርድዎ ላይ ገንዘብ ለመሙላት፡-**




- በሜትሮሬል (Metrorail) የሚገኙ የክፍያ ማሽኖችን ወይም የማለፍያ ማሽኖችን ወይም የሜትሮ ባስ የመክፈያ ማሽኖችን በመጠቀም ወይም ተሳታፊ በሆኑ መሸጫ ቦታዎች ውስጥ መሙላት ይችላሉ። (ቦታዎችን ለማወቅ ይህን ድረ-ገጽ ይመልከቱ wmata.com)
- በማሽኑ ላይ ካርድዎን በትእዛዙ መሰረት በማስነካት መመሪያዎቹን ይከተሉ።
- ገንዘብ ወይም የፌር ካርድ (farecard) ያስገቡ (ዋጋው $20 ወይም ከዚያ በታች)።በተጨማሪም Visa፣ MasterCard፣ Discover፣ American Express ወይም ATM ካርድ ሊጠቀሙ ይችላሉ (እያንዳንዱ ግዢ(transaction) ለየብቻው ሊካሄድ ይገባል)።
- የሚያዩት አዲስ የገንዘብ መጠን ካርዱ ውስጥ እንዲኖር የሚፈልጉት ያህል እስከሚሆን ድረስ የመደመር (+) ወይም የመቀነስ (-) ምልክቶችን ይንኩ።በፌር ካርድ ( farecard) ካርድ ላይ የሚጨምሩ ከሆነ የተጨመረው የገንዘብ መጠን የፌር ካርድን (farecard) ለመተካት ከሚያስፈልገው ዋጋ ማነስ አይችልም።
- ካርዱን ለመጨረሻ ጊዜ ማሽኑ ላይ ያስነኩ።ይህም ካርዱን ያድሳል እና አዲሱን የገንዘብ መጠን ያሳያል።በተጨማሪም በፌርካርድ (Farecards) ላይ የ 1 ቀን የ 7 ቀን የሜትሮሬል (Metrorail) ማለፊያ በመጨመር ማሽኖቹን ማለፍ ይችላሉ።

**ክፍያዎትን በስማርት ትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ መክፈል፡-**

- በሜትሮሬል (Metrorail) ፌርጌት (faregate) ላይ እና የአውቶብስ ክፍያ ማሽን ላይ እና የሜትሮሬል (Metrorail) ጣቢያ መኪና ማቆሚያ ላይ በሚገኘው የመውጫ /የመግቢያ ማሽን ላይ ካርድዎን ያስነኩ።
- ትክክለኛው መጠን የስማርት ካርድ(SmartBenefits) ውስጥ ከተቀመጠው ዋጋ ይቀነሳል ወይም የጉዞው ማለፊያ ይረጋገጣል።
- ተሳፋሪ በሚበዛበትም ሆነ በማይበዛበት ጊዜ ወደ ሜትሮሬል (Metrorail) ለመግባት በትንሹ የ 2.25 ዶላር ክፍያ ያስፈልጋል።

**ማስታወሻ፡-** አካውንቶን በሚከተለው ድረ-ገጽ ላይ መከታተል ይችላሉ፡- smartrip.com.

## ዝውውሮች

- ከራይድ ኦን (Ride On) ወደ ሜትሮባስ (Metrobus) ወይም ሜትሮሬል (Metrorail) ሲዟዟሩ ምንም ቅናሾች የሉም።
- ከጁን 29 2025 ጀምሮ በራይድ ኦን (Ride On) ዜሮ ታሪፍ ፖሊሲ መሰረት ከሜትሮ ባስ(Metrobus) ወይም ከሜትሮሬል (Metrorail) ወደ ራይድ ኦን (Ride On) የሚደረጉ ዝውውሮች ነፃ ይሆናሉ።
- ለሜትሮባስ እና ሜትሮሬል ክፍያ ያስፈልጋል።
- ተሳፋሪዎች በ 2 ሰአት ጊዜ ውስጥ ከሜትሮባስ (Metrobus) ወደ ሜትሮባስ (Metrobus) ነፃ እና ያልተገደበ ዝውውሮችን ለማግኘት የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ መጠቀም አለባቸው።
- ተሳፋሪዎች በ 2.25 ሰአት ጊዜ ውስጥ ከሜትሮባስ ወደ ሜትሮሬይል ወይም ከሜትሮሬል ወደ ሜትሮባስ ሲሸጋገሩ የ $2 ቅናሽ ለማግኘት የስማርትሪፕ (SmarTrip®) ካርድ መጠቀም አለባቸው።
- ተሳፋሪዎች ወደ ወይም ከኤክስፕረስ ሜትሮ (express Metro) መስመሮች ሲተላለፉ የ $2.25 ቅናሽ ለማግኘት የስማርትሪፕ (SmarTrip) ካርድ መጠቀም አለባቸው።

## ታይትል 5 (Title VI)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በማንነት ምክንያት፣ በ 1964 የሲቪል መብቶች ህግ ታይትል 5 እና በ 1987 የሲቪል መብቶች ህግ እንደተደነገገው ማንኛውም ግለሰብ ፣ከየትኛውም ፕሮግራም ወይንም የስራ ዘርፍ አገልግሎት ከማግኘት እንደማይገለል፣ እንደማይከለከል እና በማንኛውም መንገድ መድሎ እንደማይፈጸምበት ያረጋግጣል።ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የሚከተለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡ http://www.montgomerycountymd.gov/DOT-Transit/titlevi.html.

## ጥያቄዎች፣ አስተያየቶች፣ ምስጋናዎች እና ቅሬታዎች

የኤምሲዲኦቲ (MCDOT) አገልግሎት ጥያቄ፣ ቅሬታ ወይም ምስጋና ለማቅረብ በ 311 ይደውሉ።ከካውንቲው ውጪ ሲደውሉ በ 240-777-0311 ይደውሉ ወይም በ MC311 ድረ-ገጽ በኩል ያስገቡ፣www.montgomerycountymd.gov/mc311። እባክዎ የአውቶብሱን መንገድ ቁጥር፣ ቀን፣ ሰአት፣ ስፍራ እና መዳረሻ ያቅርቡ።

በአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ህግ (American with Disabilities, ADA) አስፈላጊ የራይድ ኦን አገልግሎት ለማግኘት ተጨማሪ አገልግሎት የሚያስፈልግዎ ከሆነ MC311 በድምጽ በ 240-777-0311 TTY 711፣ ወይም በሚከተለው ኢሜል ይጠቀሙ።
RideOn.CustomerService@montgomerycountymd.gov